አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like the River

ቁጥር-16, ጥር 2013 ዓ.ም
Issue No. 16, January 2021

# አዋሽ ዜና መጽሔት
# Awash Newsletter

በማርኬቲንግና ኮምዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት የሚታተም
Published by: Marketing & Communication Directorate



8980
contactcenter@awashbank.com
www.awashbank.com

# በዚህ ዕትም


**የአዋሽ ባንክ ዋና ሥራ አሥፈጻሚ መልዕክት** .......... 1

**አዋሽ ባንክ ከሬይስ ማይክሮ ፋይናንስ ጋር አብሮ መስራት የሚያስችለውን የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረመ** .......... 2

**የአዋሽ ባንክ** 25**ኛው ዓመታዊ የባለአክስዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ተካሄደ** .......... 3

**አዋሽ ባንክ ተቋማዊ መዋቅራዊ ለውጥ አደረገ** .......... 5

**የአዋሽ ሠራተኞች የብድር አሰጣጥ ላይ ማሻሻያ ተደረገ** .......... 7

**አዋሽ ባንክ ለሀገር መከላከያ ሠራዊትና ህግ በማስከበር ወቅት ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖቻችን የሚውል የብር** 10 **ሚሊዮን ድጋፍ አደረገ** .......... 7

**አዋሽ ባንክ በአሰላ ከተማ አዲስ ህንፃ ሊገነባ ነው** .......... 8


# In This Issue


Articles .......... 10

Proverbs & Quotes .......... 18



**ዋና አዘጋጅ**

ተሾመ ዋቅጅራ

**ረዳት አዘጋጆች**

ድሪባ መገርሳ

ሰላም ተክለጽዮን

**ፎቶግራፍ**

ዳንኤል ምትኩ

**ግራፊክ ዲዛይነር**

ቱሪ እስማኤል

**EDITOR-IN-CHIEF**

Teshome Wakjera

**ASSISTANT EDITORS**

Deriba Megerssa

Selam Tekletsion

**PHOTOGRAPHER**

Daniel Mitiku

**GRAPHIC DESIGNER**

Turi Ismael

# የአዋሽ ባንክ ዋና ሥራ አስፈፃሚ መልዕክት



አቶ ፀሀይ ሽፈራው
የአዋሽ ባንክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ

## ውድ የአዋሽ ባንክ ቤተሰቦች

ባንካችን የቪዥን 2025 እስትራቴጂ ነድፎ እየተንቀሳቀሰ ከመሆኑም በላይ ገናና ስሙን አስጠብቆ ከአስር ሺህ በላይ ለሆኑ ዜጎች የሥራ እድል መፍጠር የቻለ ባንክ በመሆኑ ሁላችንም ልንኮራ ይገባናል። አዋሽ ባንክ ባለፉት ዓመታት በተለይም ደግሞ ባለፉት አምስት አመታት ውስጥ አመርቂ ውጤት በማስመዝገብ እጅግ ተመራጭና ጠንካራ ባንክ በመሆንና በሀገር ውስጥ ካሉ የግል ባንኮች በፍጥነት ያደገ ከመሆኑም ባሻገር ለባለአክስዮኖቻችንም ጠቀም ያለ ትርፍ በማስገኘት እንዲሁም ለመንግስትም በሚሊዮን የሚገመት ግብር በመክፈል በፌደራል መንግስት ደረጃ የፕላቲኒየም ተሸላሚ ለመሆን የበቃ  የህዝብ  ባንክ ነው።

የባንኩ ባለአክስዮኖች ተነጋግረው ለዳይሬክተሮች ቦርድ ባቀረቡት ሃሳብና ቦርዱ በወሰነው ውሳኔ መሰረት ለባንኩ ከፍተኛ የማኔጅመንት አባላት ባለፉት አስርት አመታት ባስመዘገቡት ከፍተኛ የሥራ አፈጻጸም እውቅና እንዲሰጣቸው ተደርጓል። በዚህም መሰረት ለባንኩ ከፍተኛ የሥራ ሀላፊዎች የእውቅና አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት ህዳር 10 ቀን 2013 ዓ.ም በሒልተን አዲስ አበባ ሆቴል ተከናውኗል።

ይህ ተደናቂ የሥራ ውጤት የተገኘው ከበላይ የሥራ ሀላፊዎች አመራር ብቻ ሳይሆን በብዙሃን የማኔጅመንት አባላትና በመላው የአዋሽ ባንክ ሠራተኞች ጥረት ስለሆነ የእውቅና አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓቱ በተዋረድ ወደ ታችኛው የማኔጅመንት እርከን እንዲወርድ የባንካችን የቦርድ ዳይሬክቶሬት በወሰነው ውሳኔ መሰረት የሃምሳ ሺህ አራት መቶ አክስዮኖች የግዥ ወጪንና ተያያዥ ሰላሳ ፐርሰንት ግብር ባንኩ ከፍሎ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ለተመረጡት የባንኩ የመካከለኛ የማኔጅመንት አባላትና እስከ ሲኒየር ኦፊሰር የሥራ መደብ ለሚገኙ ሠራተኞች እንደየስራ ሃላፊነታቸውና የአገልግሎት ዘመናቸው አክስዮኖች በነፍስ ወከፍ ተደልድሎላቸው የእውቅና ሽልማት ተሰጥቷቸዋል። በዚህም የእድሉ ተጠቃሚ ለሆናችሁ ሁሉ እንኳን ደስ አላችሁ ለማለት እፈልጋለሁ።

## ውድ የአዋሽ ባንክ ቤተሰቦች

ስጦታ በተፈጥሮ የፍቅር መገለጫ ነው ! በዚህ አስጨናቂ ወቅት ደግሞ እኛን በማሰብና ይገባቸዋል ብሎ በመወሰን የተደረገው የአክስዮን ድልድል የሥራ ተነሳሽነታችንን ከመጨመሩም በላይ ለባንካችን እራሳችንን እንድንሰጥ ምክንያት እንደሚሆነን ጭምር ጥርጥር የለኝም። በተጨማሪም ይህ ማበረታቻ ከፊታችን የሚጠብቀንን ፈተና በብቃት ለመቋቋምና ለበለጠ ክንውን ለመዘጋጀት የሞራል ስንቅ እንዲሆነን የተሰጠን ስጦታ መሆኑን መረዳት ይገባናል።

ባለፉት ዓመታት በተቀማጭ ገንዘብ፣ በብድር፣ በካፒታል እድገት እንዲሁም በቅርንጫፎች ብዛት የቀዳሚውን ስፍራ አስጠብቆ የቆየው ባንካችን በሚቀጥሉት አምስት አመታትና በቀጣይም እንደተለመደው ይህንኑ ቀዳሚነት ስፍራውን አስጠብቆ በምስራቅ አፍሪካ ካሉት አስር ስመጥር ባንኮች ተርታ ለመሰለፍ በከፍተኛ ወኔ በመንቀሳቀስ የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ እንዳለብን በአጽዕኖት ማስገንዘብ እወዳለሁ። ይህንኑ ራዕያችንን እውን ለማድረግ በቦርድ ፀድቆ የተሰራጨውን የ2020/21 የሥራ እቅድ ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚ ለማድረግ በሁሉም ረገድ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ማድረግ ከሁላችንም የሚጠበቅ ሲሆን ለአፈጻጸሙም የተለያዩ መዋቅራዊና ስልታዊ የስትራቴጂ ውሳኔዎች በአሁኑ ወቅት እየተወሰዱ ይገኛሉ፡ ፡ ምንም እንኳ በዓለማችን ላይ የተከሰተው የኮሮና ቫይረስ ተጽዕኖ፣ የሀገራችን የሰላም ሁኔታ እንዲሁም በባንኮች መካከል የሚታየው ከፍተኛ ውድድር እጅግ ከባድ ቢሆንም ይህንኑ ፈታኝ ሁኔታ በጠንካራው ማኔጅመንትና በታታሪ ሠራተኞቻችን ብርታት ተቋቁመን በአሸናፊነት እንድምንወጣ ምንም አልጠራጠርም። የአንድ ድርጅት ስኬት ትልቁ ቁልፍ የሰው ሀይል ሲሆን የሰራን ማመስገን ለወደፊትም  የተሻለ ሥራ እንዲሰራ ማበረታቻዎችን መስጠት ደግሞ የእኔነትን፣ የባለቤትነትንና የተነሳሽነትን ስሜት እንደሚፈጥርባችሁ በመተማመን በመጨረሻም በተለመደው የሥራ ባህላችን እቅዶቻችንን ሁሉ በጋራ በማሳካት ለቀጣይ ድል እንድንዘጋጅ ለማሳሰብ እወዳለሁ። አመሰግናለሁ ! !

# አዋሽ ባንክ ከሬይስ ማይክሮ ፋይናንስ ጋር አብሮ መስራት የሚያስችለውን የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረመ



የመግባቢያ ሰነዱ የፊርማ ሥነ-ሥርዓት በከፊል

የመግባቢያ ስምምነቱን የፈረሙት የአዋሽ ባንክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ፀሀይ ሽፈራው እና የሬይስ ማይክሮ ፋይናንስ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ አብዲአዚዝ ሀሰን ሲሆኑ ስምምነቱ በርካታ የፋይናንስ ስራዎችን በትብብር ለመስራት የሚያስችል መሆኑን የሁለቱ ተቋማት ኃላፊዎች ገልጸዋል። የመግባቢያ ስምምነቱ ዋና ዓላማ ባንኩ ተደራሽነቱን በማስፋት እንዲሁም ከሬይስ ማይክሮ ፋይናንስ ጋር በመተባበር ማይክሮ ፋይናንሱ በሰፊው በሚንቀሳቀስባቸው በምስራቁ የሀገሪቱ ክፍል ለሚገኙና የባንክ አገልግሎት ተጠቃሚ ላልሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች እንደየአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ በቴክኖሎጂ የታገዘ አስተማማኝ የፋይናንስ አገልግሎት መስጠት እንደሆነም ተጠቁሟል።

# የአዋሽ ባንክ 25ኛው ዓመታዊ የባለአክስዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ተካሄደ

የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ የባለአክሲዮኖች 25ኛ ጠቅላላ ጉባኤ ህዳር 19 ቀን 2013 ዓ.ም በአዲስ አበባ ሒልተን ሆቴል ተካሂዷል። ባንኩ ባካሄደው 25ኛው ዓመታዊ የባለአክስዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ እንዳስታወቀው በ 2012 የሂሳብ ዓመት አመርቂ ውጤት ማስመዝገቡንና ለውድ ደንበኞቹ ተደራሽ በሚያደርጋቸው የተለያዩ አይነት የባንክ አገልግሎቶች ያገኘው ጠቅላላ ውጤት በግል ባንኮች ታሪክ ከፍተኛው መሆኑን የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ክቡር አምባሳደር ዶ/ር ዲባባ አብደታ በሪፖርታቸው ገልጸዋል።

የኮሮና ቫይረስ በአለም አቀፍ ደረጃ የኢኮኖሚ ቀውስ እያስከተለ ቢሆንም አዋሽ ባንክ በአስር ዓመቱ ፍኖተ ካርታው ላይ ባስቀመጠው ስትራቴጂ በመመራትና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ቀውሶችን ለመቆጣጠር የሚያስችሉትን ስትራቴጂዎችን በመተግበር የበጀት ዓመቱን በአመርቂ ውጤት ማጠናቀቁን ጭምር የቦርድ ሰብሳቢው ለጠቅላላ ጉባኤው ገልፀዋል። እንደ ዳይሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበር ገለፃ አዋሽ ባንክ በሀገሪቱ የፋይናንስ ኢንዱስትሪ ውስጥ አዳዲስ ታሪኮችን አስመዝግቦበታል ተብሎ ከተገለጸው ውስጥ በዋናነት አመታዊ የትርፍ መጠን ተጠቃሽ ነው።



ክቡር አምባሳደር ዶ/ር ዲባባ አብደታ የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ በጉባኤው መክፈቻ ላይ ንግግር ሲያደርጉ

ያለፈው በጀት ዓመት በዓለማችን ከተከሰተው የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ የተነሳ ለአገሪቱ ኢኮኖሚ በአጠቃላይ ለባንኪንግ ኢንዱስትሪው ደግሞ በተለየ ሁኔታ ፈታኝ ከመሆኑም በተጨማሪ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የሚሄደው የዋጋ ንረት፣በተለያዩ የአገራችን ክፍሎች የነበሩ የፖለቲካ አለመረጋጋቶችና የፀጥታ ስጋት፣በባንኮች መካከል ያለው ከፍተኛ ፉክክር እያደገ የመጣበት ዓመት የነበረ ቢሆንም አዋሽ ባንክ ያስመዘገበው አኩሪ ውጤት ከቀደሙት ዓመታት እጅጉን የላቀ እንደነበር የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢው ገልፀዋል።

አዋሽ ባንክ በየጊዜው የሚያስመዘግባቸው ተከታታይ ዕድገቶች ባንኩን በጠንካራና አስተማማኝ መሠረት ላይ እያቆሙት መሆኑንም የቦርድ ሰብሳቢው ጠቁመዋል። ይህ አመርቂ ውጤት ሊገኝ የቻለው የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድና የስራ አመራር አባላት ተቀናጅቶ መስራትና በየደረጃው ያሉ የባንኩ ሠራተኞች ባሳዩት ከፍተኛ የስራ ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት ነው ያሉት አምባሳደር ዶክተር ዲባባ አብደታ፣ለዚህም የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ላበረከቱ ባለድርሻ አካላት ሁሉ ምስጋና አቅርበዋል። የአዋሽ ባንክ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ፀሐይ ሽፈራው በበኩላቸው 2019/20 የሂሳብ በጀት ዓመት አዋሽ ባንክ የኮሮና ቫይረስ

ወረርሽኝ በአገር አቀፍ ደረጃ በተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች ላይ የሚያደርሰውን ተፅዕኖ ለመቀነስና ለመቋቋም መንግስት ለሚያደርገው ጥረት ተገቢውን ድጋፍ በማድረግ ህዝባዊነቱን ያስመሰከረበት ዓመት ከመሆኑም ባሻገር ባስመዘገበው ዓመታዊ ትርፍም ለአምስተኛ ጊዜ መሪነቱን አረጋግጧል ብለዋል።ባንኩ ወረርሽኙ ቀጥተኛ ተፅዕኖ ላሳረፈባቸው በተለይ የሆቴል፣ የአበባና አስጎብኚ ድርጅቶች የተለያዩ እፎይታዎችን በማድረግ ቢዝነሳቸው ለከፋ ችግር እንዳይጋለጥ ለማድረግ ተችሏል። የባንኩ ደንበኞችና ሠራተኞችን ከወረርሽኙ ለመከላከልም ኮሚቴ በማዋቀር በሚሊዮኖች የሚገመት ገንዘብ በማፍሰስ የተለያዩ የመከላከያ ግብዓቶችን የማቅረብና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ሰርቷል። በአገር አቀፍ ደረጃም ለመንግስትና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች ከ11 ሚሊዮን ብር በላይ የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ለወረርሽኙ ሰለባዎች ሰብዓዊ ዕርዳታ እንዲደርስ ማድረጉንም አቶ ፀሐይ አስረድተዋል።



አቶ ፀሀይ ሽፈራው የአዋሽ ባንክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በጉባኤው  ላይ ንግግር ሲያደርጉ

አዋሽ ባንክ 2019/20 የሂሳብ ዓመት ማጠቃለያ ላይ፡-

- በተቀማጭ ገንዘብ የ19 በመቶ ዕድገት በማስመዝገብ ብር 74.3 ቢሊዮን ደርሷል።
- በብድር የ21 በመቶ ዕድገት በማስመዝገብ ለተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች የተሰጠው ብድር ብር 57.3 ቢሊዮን ደርሷል። በአንፃሩ ደግሞ የባንኩ የተበላሸ ብድር ምጣኔ በበጀት ዓመት ማጠቃለያ ላይ 1.7 በመቶ ነበር። ይህ ብሔራዊ ባንክ ካስቀመጠው የአምስት በመቶ ምጣኔ አንፃር ሲታይ የአዋሽ ባንክ ብድር ጤነኛና በአስተማማኝ ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ያሳያል።
- በበጀት ዓመቱ ማጠቃለያ የባንኩ አጠቃላይ የሀብት መጠን የ19.7 በመቶ ዕድገት በማስመዝገብ ብር 89.3 ቢሊዮን የደረሰ ሲሆን፣
- የባንኩ የተከፈለ ካፒታል ደግሞ እ.ኤ.ኤ.  ሰኔ 30 ቀን 2019 ከነበረበት ብር 4.38 ቢሊዮን የብር 1.46 ቢሊዮን ወይም የ33.4 በመቶ ዕድገት በማሳየት እ.ኤ.አ ሰኔ 30 ቀን 2020  መጨረሻ ላይ ብር 5.85 ቢሊዮን ደርሷል። በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ የባንኩ የተከፈለ ካፒታል ብር 12 ቢሊዮን እንደሚደርስ ይጠበቃል።
- በአጠቃላይ የትርፍ መጠን የስምንት በመቶ ዕድገት በማሳየት የብር 3.6 ቢሊዮን ዓመታዊ ትርፍ ማስመዝገቡንም ገልፀዋል።

በሌላ መልኩ  በ2019/20 የሒሳብ ዓመት አዋሽ ባንክ፡-

- በጅማ ከተማ  ባለ ስድስት ወለል ህንፃ በማስመረቅ ለአገልግሎት አብቅቷል፤ በአዲስ አበባ የቡልቡላ ቅርንጫፍ እና በባሌ ሮቤም የአዳዲስ ህንፃዎች ግንባታ አስጀምሯል።
- የባንኩን ሰራተኞች አቅም ለመገንባት ሲባል በባንኩ የስልጠና ክፍል፣ በአገር ውስጥና ከአገር ወጪም ስልጠናዎችን በተሳካ ሁኔታ ሰጥቷል።
- በበጀት ዓመቱ ከ1.3 ቢሊዮን ብር በላይ ግብር በመክፈል የዓመቱ ታማኝና ከፍተኛ ግብር ከፋይ በመባል በፕላቲኒየም ደረጃ በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ (ዶ/ር) የዕውቅና ሽልማት  ተበርክቶለታል።

# አዋሽ ባንክ ተቋማዊ መዋቅራዊ ለውጥ አደረገ

አዋሽ ባንክ በየጊዜው ፈጣን ለውጥ እያሳየ ከሚሄደው የዘርፉ አሰራር ጋር ለመራመድ የሚያስችለውንና በአስር ዓመታት ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ ያቀደው የባንኩን ቪዥን 2025ን ባቀደው መሰረት ለመተግበር የሚያስችለውን አዲስ ተቋማዊ የመዋቅር ለውጥ አደረገ።

አዋሽ ባንክ እስከ አሁን ድረስ ሲተገብር የነበረውን ተቋማዊ አደረጃጀትን ኬፒኤምጂ ኢስት አፍሪካ (KPMG East Africa) በሚባል የውጭ አማካሪ ድርጅት ያሰራ ሲሆን እ.ኤ.አ 2015/16 ጀምሮ ላለፉት አምስት ዓመታት ሲሰራበት ቆይቷል።

ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ በባንኪንግ ኢንዱስትሪው ውስጥ ከተስተዋሉት ፈጣን ለውጦች ጋር የሚጣጣም መጠነኛ የመዋቅር ክለሳዎች ቢደረጉም፣ ዘርፉ አሁን ከደረሰበት ዕድገት እና በፋይናንስ ኢንዱስትሪው ውስጥ ካለው ፈጣን ለውጥ ጋር ለማጣጣም በሚችል መልኩ መሰረታዊ የመዋቅር ለውጥ ማድረግ በማስፈለጉ ባንኩ አዲስ ተቋማዊ የመዋቅር ለውጥ አድርጓል።

አዋሽ ባንክ ደንበኞቹን በቅርበት ለመከታተል፣ ሙያዊ ድጋፍ ለመስጠትና አዳዲስ ደንበኞችንም ባሉት አማራጭ የአገልግሎት ዘርፎች ላይ በቂ ግንዛቤ በመስጠት ወደ ደንበኝነት ለማምጣት የሚያስችለውን የሪሌሽን ሺፕ ማኔጅመንት (Relation-ship management) ስርዓት ዘርግቶ ሲጠቀምበት ቆይቷል።

ባንኩ አሁን ተግባራዊ ያደረገው አዲሱ ተቋማዊ የመዋቅር ለውጥ አሁን ከደረሰበት የዕድገት ደረጃ እና በዘርፉ ውስጥ በየጊዜው የሚታዩ አዳዲስ ለውጦችን ተቀብሎ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ከመሆኑም ባሻገር ለባንኩ ዕድገትና ውጤታማነት ብሎም እስከ ዛሬ በመሪነት እንዲቀጥል ያስቻለውን የደንበኞች እርካታን ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ የተዘጋጀ ነው።

በዚሁ መሰረት በዋና መስሪያ ቤት ደረጃም የስራ እንቅስቃሴ ባማከለ እና በተቀላጠፈ ሁኔታ ለመስራት የሚያስችል አደረጃጀት ተፈጥሯል። በዚህም መሰረት ቀደም ሲል አምስት የነበረው የቺፍ ኦፊሰሮች ቁጥር ወደ ሰባት፣ ሶስት የነበረው ዲፒዩቲ ቺፍ ኦፊሰሮች ቁጥር ወደ ስድስት፣ ሃያ ሁለት የነበረው የዳይሬክተሮች ቁጥር ወደ 31 እንዲያድግ ተደርጓል። በሌላ መልኩ ቀደም ሲል በስራአስኪያጅ (Manager) ደረጃ የነበሩት የቀጠና ጽ/ቤቶች የማስፈፀም አቅማቸውን የበለጠ ለማጎልበት ሲባል ወደ ዳይሬክተር (Director) ደረጃ ከፍ እንዲሉ ተደርጓል።

ይህም በቀጠና ጽ/ቤቶች ደረጃ ለደንበኞች የሚሰጡ አገልግሎቶች እንዲቀላጠፉና ደንበኞች በአገልግሎቶቻችን እንዲረኩ ታስቦ የተደረገ መዋቅራዊ ለውጥ ነው። መዋቅራዊ ለውጡ ከዋና መስሪያ ቤት እስከ ቅርንጫፎች ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን፣ በአዲሱ አደረጃጃት ሁሉም የባንኩ ቅርንጫፎች በስራአስኪያጆች እንዲመሩ ተደርጓል። አዲስ ስራ ላይ እንዲውል በተደረገው ተቋማዊ አደረጃጀት በዋና መስሪያ ቤት፣ በቀጠና ጽ/ቤቶች እንዲሁም ቅርንጫፎች የባንኩ የሰው ኃይል በ1770 የሚጨምር ሲሆን የዚህ ሁሉ መሰረታዊ ዓላማ በየደረጃው የሚሰጡትን አገልግሎቶች በማቀላጠፍና በማዘመን አዋሽ ባንክን ተወዳጅና ተመራጭ እንዲሁም የዘርፉ መሪ እንዲሆን ማስቻል ነው።

ልዩ የተማሪዎች የቁጠባ ሂሳብ

# Student
## Saving Account

" ዛሬን ለነገ "



አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like The River

# የአዋሽ ባንክ ሠራተኞች የብድር አሰጣጥ ላይ ማሻሻያ ተደረገ

አዋሽ ባንክ የአገልግሎት አሰጣጡን ከማዘመንና ተደራሽነቱን ከማስፋት ባሻገር ከአስር ሺህ በላይ ለሚደርሱ ሠራተኞቹ ልዩ ትኩረት በመስጠት እንዲሁም አሁን ላይ ያለውን የሀገሪቱን ወቅታዊ የኢኮኖሚ ሁኔታና የዋጋ ግሽበትን ከግምት ውስጥ በማስገባት ለሠራተኞቹ በሚሰጠው የብድር አገልግሎት ላይ ከፍተኛ የሚባል ማሻሻያ አድርጓል።

የብድር አሰጣጥ ማሻሻያው የተደረገው በዋናነት በመኖርያ ቤት ግዢ፣ የመኪና ግዢ እና (personal Loan) ላይ ነው።

በዚህም መሰረት የቤትና መኪና ግዢ ለመውሰድ የሚያመለክት ማንኛውም ሠራተኛ የብድሩ መጠን እንደየሠራተኛው የተጣራ ደሞዝ የሚወሰን እንዲሆን ተደርጓል። የወለድ ምጣኔውም ወደ ሰባት በመቶ ዝቅ እንዲል ተደርጓል፣ ይህም የሠራተኛውን ተጠቃሚነት ከማረጋገጡም በላይ በሠራተኛው ዘንድ ጠንካራ የሥራ ተነሳሽነትና የባለቤትነት ስሜት ይፈጥራል ተብሎ ይታመናል።

# አዋሽ ባንክ ለሀገር መከላከያ ሠራዊትና ህግ በማስከበር ወቅት ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖቻችን የሚውል የብር 10 ሚሊዮን ድጋፍ አደረገ

በሀገራችን ኢኮኖሚ ውስጥ ጉልህ ሚና እየተጫወተ ያለውና ኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነቱን በተለያዩ ዘርፎች እየተወጣ የሚገኘው አዋሽ ባንክ የሀገሪቱን ወቅታዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ እንዲሁም በባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድና የሥራ አመራር ውሳኔ መሰረት ለሀገር መከላከያ ሠራዊትና ህግ በማስከበር ወቅት ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖቻችን የሚውል የብር 10 ሚሊዮን ድጋፍ አድርጓል። የመከላከያ ሰራዊትን በመወከል በባንኩ የተበረከተውን ድጋፍ የተረከቡት የሀገር መከላከያ ሠራዊት የውጭ ግንኙነት ኃላፊ ኮሎኔል የኑስ ሙሉ አዋሽ ባንክ ያደረገው የገንዘብ ድጋፍ ለሰራዊቱ ከፍተኛ የሞራል ስንቅ እንደሚሆን ገልጸው በመከላከያ ሠራዊቱ ስም ልባዊ ምስጋናቸውን አቅርበዋል። ኃላፊው ሠራዊቱ በክፉም በደጉም ከህዝቡ ጎን ሲቆም መኖሩን አስታውሰው ወደፊትም በቁርጠኝነት ለህይወቱ ሳይሳሳ ለሀገራችን ሉአላዊነት መከበር መዋደቁን እንደሚቀጥል አረጋግጠዋል።

የሀገር መከላከያ ሠራዊት የህግ ማስከበር ዘመቻ ላይ መሠማራቱን ተከትሎ ለሠራዊቱ እና በህግ ማስከበር ዘመቻው ሂደት ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች ማቋቋሚያ የሚሆን የአንድ ወር ደሞዛቸውን እና የደም ልገሳ በማድረግ ያስጀመሩት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ ወ/ሮ አዳነች አቤቤ በበኩላቸው በድጋፍ ርክክብ ሥነ-ስርዓቱ ላይ ባደረጉት ንግግር አዋሽ ባንክ ላደረገው ከፍተኛ ድጋፍ በራሳቸውና በከተማ አስተዳደሩ ስም ከፍ ያለ ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

የሀገር መከላከያ ሠራዊት በህዝብ የተጣለበትን ኃላፊነት እንዲወጣ የሚያደርገው ዋነኛው ምክንያት የህዝብ ድጋፍ እና ሞራል መሆኑን የገለፁት ወ/ሮ አዳነች አቤቤ አሁን በሀገራችን የተከሰተው ችግር ከተሰማበት ጊዜ ጀምሮ በሁሉም ሥፍራ ህዝቡ ያደረገው ድጋፍና የተደረገው ንቅናቄ በታሪክ ውስጥ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው መሆኑን አስገንዝበዋል። ሠራዊቱም ከጎኑ፣ ከፊቱና ከኋላው የተሰለፈውን ህዝብ መሠረት ያደረገ ተጋድሎ እንደሚያደርግ ያላቸውን ጽኑ እምነት ገልፀዋል።

አዋሽ ባንክ ከምስረታው ጀምሮ የፋይናንስ አገልግሎቱን ተደራሽ ከማድረጉም ባሻገር ኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነቱን በሚገባ በመወጣት ላይ እንደሚገኝና በቀጣይም ከመንግስት ጎን በመቆም ጉልህ ድርሻ እንደሚጫወት ተጠቁሟል።

# አዋሽ ባንክ በአሰላ ከተማ አዲስ ህንፃ ሊገነባ ነው




በአዲሱ የአሰላ ከተማ ሕንጻ እንዲሁም የተወዳዳሪዎች ዲዛይን ዙርያ የተደረገ ጉብኝት

በአዲስ አበባ እና በተለያዩ የክልል ከተሞች የራሱን ህንፃ በመገንባት የሚታወቀው አዋሽ ባንክ በአሰላ ከተማ ባለ አምስት ፎቅ አዲስ ዘመናዊ ህንፃ ለመገንባት የህንፃውን አርክቴክቸራል ዲዛይን ስራ አጠናቋል። ባንኩ የህንፃውን አርክቴክቸራል ዲዛይን ለማሰራት ባወጣው ጨረታ ተወዳድሮ ላሸነፈው አማካሪ ድርጅትም የእውቅና ሰርቲፍኬት እና የገንዘብ ሽልማት አበርክቷል። ሌሎች ተወዳዳሪ ድርጅቶችንም ለማበረታታት ሲባል ከአንደኛ እስከ አምስተኛ ለወጡት ተወዳዳሪዎች ከብር 100 ሺህ እስከ 25ሺህ የገንዘብ ሽልማትና የእውቅና ሰርቲፍኬት በባንኩ ተበርክቶላቸዋል።

አዲሱ የአዋሽ ባንክ አሰላ ቅርንጫፍ ህንፃ ግንባታም በቅርቡ እንደሚጀመርና በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጠናቆ ለአገልግሎት እንደሚውል የባንኩ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ፀሐይ ሽፈራው ተናግረዋል።






የሕንጻው ዲዛይን አሸናፊና ተሳታፊዎች የእውቅናና የሽልማት አሰጣጥ መርሐ-ግብር በከፊል

አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like the River



# የልጆች የቁጠባ ሳጥን ተጠቃሚ ይሁኑ!

አዋሽ ባንክ በዓይነቱ ልዩ የሆነ የልጆች የቁጠባ ሳጥን ተጠቃሚ እንዲሆኑ በሁሉም ቅርንጫፎቹ አቅርቦሎታል። ከልጆችዎ የቁጠባ ሂሳብ ከፍተው የቁጠባ ሳጥን በመውሰድ እየጨመረ የሚሄድ የወለድ ምጣኔ ተጠቃሚ ይሁኑ!



SMART
Children

# Some Cyber Security Tips



Cyber threats are a global risk that governments, the private sector, non-governmental organizations – and the global community as a whole – must deal with.

Fraudulent emails may be designed to appear as though originates them. Do not respond to any email communications, which request any type of personal or confidential information and do not go to any links listed on that email.

**MOBILE BANKING SECURITY AWARENESS**

Mobile Banking allows you to bank anytime, anywhere from the convenience of your mobile phone. This service provides secure access to your bank accounts, allowing you to view account balances and other activity. You will also be able to search account activity, transfer funds, and perform payments. Cyber  uses multiple forms of identification authentication, login procedures and encrypted communications to make sure your mobile Banking application is safe and secure.

The continuing growth of mobile phones and mobile banking is providing conveniences for you and offers more ways to access accounts. Of course, fraudsters (those individuals trying to steal personal information) are going to follow the same path and turn their attention to mobile banking with malware and social engineering in search of potential targets.

Fraudsters know that one of the possible keys to their success lies within an account holder. Security awareness education is a key to minimizing these risks to any business customers from fraudsters.

## TIPS FOR SAFE AND SECURE MOBILE BANKING

- Research any application (App) before downloading it. Just because the name of an App resembles the name of the Bank. It could be a fraudulent app designed to trick users into believing the service is legitimate. The right place to download the campanies mobile banking App is from the App store.

- It will never ask for your password under any circumstances. Do not tell your password to others under any circumstances (including mobile phone support operators or mobile phone sales representatives, etc.). Fraudsters will try to obtain mobile Banking passwords by e-mail, letter, phone calls, asking for your mobile banking account number, username, password, and other important information.

- use strong passwords that are not easily guessable. They should be composed of numbers, letters (upper case and lower case) and special characters.

- It is good practice to change your mobile banking password regularly.

- Do not lend others your phone with the mobile banking function opened, as this will prevent infringement and deter others from spying on your personal information.

## ONLINE BANKING SECURITY

Online Banking uses several different methods to protect your information. All information within our Online Banking uses the Secure Socket Layer (SSL) protocol for transferring data. SSL is a cryptosystem that creates a secure environment for the information being transferred between your browser.

Here are some tips on keeping your information secure.

- Never give out any personal information including User Names, Passwords, SSN, and Date of Birth.
- Create strong passwords, which include Letters, Numbers, & Symbols when possible.
- Do not use personal information for your user names or passwords like Birth Dates & SSN.
- Avoid using public computers to access your Online Banking.
- Do not give any of your personal information to any web sites that does not use encryption or other secure methods to protect it.

## WHAT IS IDENTITY THEFT?

Identity theft involves the unlawful acquisition and use of someone's identifying information, such as:

- Name
- Address
- Date of Birth
- Social Security Number
- Mother's Maiden Name
- Driver’s License
- Bank or Credit Card Account Number

Thieves then use the information to repeatedly commit fraud in an attempt to duplicate your identity, which may include opening new accounts, purchasing automobiles, applying for loans, credit cards, and social security benefits, renting apartments and establishing services with utility and telephone companies. It can have a negative effect on your credit and create a serious financial hassle for you.

**HOW DO I PROTECT MYSELF?**

- Report lost or stolen checks or credit cards immediately
- Never give out any personal information including birth date, SSN or Passwords
- Do not shared all documents containing personal information, like bank statements, unused checks, deposit slips, credit card statements, pay stubs, medical billings, and invoices
- Do not give any of your personal information to any web sites that do not use encryption or other secure methods to protect it.
- Do not write your credit card password anywhere. Try to keep it on your mind. (Source: Awash Bank IT Security team)

# Impacts of COVID-19 on Global Economic Growth

is obvious that COVID-19 pandemic is inflicting high risk and rising risk human costs worldwide, and the necessary protection measures are severely impacting economic activity.

Moreover, as the World Bank claims as the result of the pandemic on the global economy is projected to contract sharply by negative three percent (-3%) in 2020 which is much worse than of the 2008-09 the global financial crisis. According to the World Bank report the pandemic may fade in the second half of 2020 in the baseline scenario and the containment efforts can be gradually unwound-the global economy is projected to grow by 5.8 percent in 2021 provided that the economic activity normalizes itself and helped by policy support.

Effective policies are essential to forestall the possibility of worse outcomes, and the necessary measures to reduce contagion and protect lives are an important investment in long-term human and economic health. Because the economic fallout is acute in specific sectors, policymakers will need to implement substantial targeted fiscal, monetary, and financial market measures to support affected households and businesses domestically. And internationally, strong multilateral cooperation is essential to overcome the effects of the pandemic, including to help financially constrained countries facing twin health and funding shocks, and for channeling aid to countries with weak health care systems.

Ethiopia, as part of global economic family, cannot escape the economic shock of the pandemic and according to the World Bank is facing a pronounced economic slowdown and an urgent balance of payments need owing to the COVID-19 pandemic.

The economy was growing robustly prior to the pandemic, and progress under the ECF-EFF arrangements was encouraging. The shock is expected to significantly reduce growth this fiscal year and next. It has already materially weakened external accounts as services exports, remittances, and foreign direct investment declined. The authorities are taking measures to combat the spread of the virus, mitigate its fallout, and support vulnerable groups. The fiscal deficit will have to expand temporarily to accommodate the additional spending.

Ethiopia launched the Homegrown Reform Agenda to address the buildup in inflation and to combat the continued foreign exchange shortages.

The report of the International Monetary Fund (IMF) shows that during the year 2019 Ethiopia’s economic growth was strong due to rapid growth shit in the service sector area than the agricultural sector.

Ethiopia’s location gives it strategic dominance as a jumping off point in the Horn of Africa, close to the Middle East and its markets. Bordering Eritrea, Somalia, Kenya, South Sudan, and Sudan, Ethiopia is landlocked, and has been using neighboring Djibouti's main port for the last two decades. However, with the recent peace with Eritrea, Ethiopia is set to resume accessing the Eritrean ports of Assab and Massawa for its

international trade.

With about 109 million people (2018), Ethiopia is the second most populous nation in Africa after Nigeria, and the fastest growing economy in the region. However, it is also one of the poorest, with a per capita income of $790. Ethiopia aims to reach lower-middle-income status by 2025.

Ethiopia's economy experienced strong, broad-based growth averaging 9.9% a year from 2007/08 to 2017/18, compared to a regional average of 5.4%. Ethiopia's real gross domestic product (GDP) growth decelerated to 7.7% in 2017/18. Industry, mainly construction, and services accounted for most of the growth. Agriculture and manufacturing made lower contribution to growth in 2017/18 compared to the previous year. Private consumption and public investment explain demand-side growth, the latter assuming an increasingly important role.

Higher economic growth brought with it positive trends in poverty reduction in both urban and rural areas. The share of the population living below the national poverty line decreased from 30% in 2011 to 24% in 2016. The government is implementing the second phase of its Growth and Transformation Plan (GTP II) which will run to 2019/20. GTP II aims to continue expanding physical infrastructure through public investments and to transform the country into a manufacturing hub. GTP II targets an average of 11% GDP growth annually, and in line with the manufacturing strategy, the industrial sector is set to expand by 20% on average, creating more jobs.

## Development Challenges

Ethiopia's main challenges are sustaining its positive economic growth and accelerating poverty reduction, which both require significant progress in job creation as well as improved governance. The government is devoting a high share of its budget to pro-poor programs and investments. Large scale donor support will continue to provide a vital contribution in the near-term to finance the cost of pro-poor programs. Key challenges are related to:

Limited competitiveness, which constrains the development of manufacturing, the creation of jobs and the increase of exports.

An underdeveloped private sector, which would limit the country's trade competitiveness and resilience to shocks. The government aims to expand the role of the private sector through foreign investment and industrial parks to make Ethiopia's growth momentum more sustainable.

Political disruption, associated with social unrest, could negatively impact growth through lower foreign direct investment,Growth in Ethiopia remained robust in FY19 thanks to a strong service sector performance. A Homegrown Reform Agenda was launched to address the buildup in inflation and persistent foreign exchange shortages. Escalating impacts of COVID-19 is expected to result in a significant slowdown in growth in FY20. While poverty is expected to continue its steady decline, the rate of reduction is likely to slow down in the short term in light of the high inflation and increased unemployment.

Real GDP growth rebounded to 9 per-cent in FY19, according to official estimates, while intermediate indicators for the first few months of FY20 paint a mixed picture. While growth in agriculture production eased and electricity production was affected by low water levels,

growth picked up in FY19 thanks to a strong service sector performance. During the first quarter of FY20 there was an exceptional increase in electricity production, but a slowdown in cement sales (-11.7 percent in Q1) and a 28 per-cent decline in FDI inflows point to a slowdown in investment.

While merchandise export performance disappointed in FY19, preliminary estimates for the first half of FY20 point to a rebound. In the first half of FY20, exports revenue increased by 10 percent com-pared to the same period last fiscal year, largely owing to a strong increase in the volume of coffee exports. The performance of the other major export commodities including oilseeds and pulses re-maimed weak, while textile exports grew by more than 45 percent. Imports of goods continued to contract declining by about 7 percent during the first half of FY20 as foreign exchange shortages persist and public investment remains restrained. Gross international reserves went down to about US$ 3 billion in December 2019, compared to US$ 3.4 billion in June.

Faster depreciation and tighter monetary policy have been implemented, while inflation remains high. Between mid- November and mid-December, the birr depreciated as much as during the entire FY19. The pace of depreciation eased in January and February. The parallel market premium has declined from 40.5 per-cent in October 2019 to about 33 percent in February 2020. The average monthly increase in reserve money was just 8.6 percent during July – December 2019, compared to 16 percent during the same period last fiscal year. Inflation eased to 19.5 in December and 18.7 percent in January, but peaked again in February, reaching 21.8 percent, with a jump in both food and non-food prices.

Despite continuing poor revenue performance, the fiscal deficit was reduced to 2.5 percent of GDP in FY19, as authorities curbed expenditure. Tax revenue collection declined to 10 percent of GDP, com-pared to 10.7 percent in FY18. This poor performance can be explained by weak tax administration and a drop in foreign trade tax revenue related to lower imports. Contained expenditures as a share of GDP and an increase in grant receipts compensated for the lower-than-expected revenue collection.

While official data is not yet available, sectors with international linkages showed already a drop in economic activity in March due to the COVID-19 pandemic. Amid the unfolding global pandemic, which is likely to bring the world economy into recession, the CEO of Ethiopian Airlines estimated revenue losses in February and March amount about USD 190 million; on March 20 the airline suspended flights to 30 countries.

Hotel occupancy has reportedly declined by 80 percent. Meanwhile, Ethiopia's cut flower industry, the second-largest ex-porter to Europe (about 10 percent of Ethiopia's merchandise export), incurred in losses amounting USD 11 million during the first weeks of March.

Increased unemployment and inflation presumably translate into slower poverty reduction in urban areas. Urban unemployment increased in 2018 to 19 percent from 17 percent in 2016. Food price inflation in excess of 20 percent has also put pressure on lower-income urban dwellers. In rural areas, which have experienced slow poverty reduction between 2011 and 2016, agricultural production levels have rebounded from the lows of the 2015/16 drought. Rural producers have likely benefited from high food prices Growth is expected to slow

down significantly in FY20 due to the impacts of COVID-19. Macroeconomic measures under the Homegrown Reform Agenda are expected to reduce imbalances and improve growth over the medium term. Growth projections have been revised down in FY20 and FY21 to reflect the Severe impacts of the COVID-19 pandemics, which is likely to place global growth in recession. The main transmission channel to Ethiopia will be through declines in services exports (air transport), the lodging industry, and cut flower and other merchandise exports. While growth is expected to be slower in the near term, economic measures under the Home-grown Reform Program are expected to set the foundations for a more balanced and stronger economy in the future. Particularly, as real exchange rate overvaluation is addressed and logistics and business environment reforms are introduced, private sector investment is expected to accelerate in FY21 and FY22. Inflation is projected to remain in double digits in FY20, prior to easing in the medium term.

Poverty is expected to continue its steady decline in the medium run on the back of reforms. The increasing industrial park development and economic reforms being under taken are expected to generate more employment opportunities, especially for the youth.

### Risks and challenges

Domestic risks include a more severe impact of the COVID-19 virus, locust infestation and political instability ahead of elections. As in other countries, the situation in Ethiopia could quickly shift from the current handful of COVID-19 imported cases to a scenario of wide-spread community transmission that could require a lockdown. In addition to the prolonged external demand impacts discussed above, this would depress domestic economic activity and demand sharply. The desert locust invasion which Ethiopia is currently experiencing is the worst in 25 years and could have an ad-verse impact on crop production in FY21. Finally, there is risk that uncertainty and tensions raise ahead of the national elections, planned for end-August, potentially hampering the prospects for FDI in-flows and delaying some of the planned privatizations. The outlook for poverty reduction, while positive, also faces significant downside risks. COVID-19 will impact the livelihoods of households dependent on remittances or linked to exporting sectors. In addition, lay-offs are expected to be dis-proportionally concentrated among low-income urban households. Currency depreciation and energy price increases are also expected to have some negative welfare effects across the distribution, especially in urban areas.

*Sources: The World Bank Website, Global Economic Outlook for the period 2020/21 and IMF WEBSITE*

# የኮሮና ቫይረስ ስርጭትን ለመከላከል ፡ -

- እጅን በንጹህ ውሃና ሳሙና አዘውትሮ መታጠብ እና አለመጨባበጥ፣
- አካላዊ ርቀትን በመጠበቅ ከሌሎች ሰዎች ጋር የሚኖርን አላስፈላጊ ንክኪን ማስወገድ፣
- ሳል ወይም ትኩሳት ካለው ግለሰብ ቢያንስ ሁለት እርምጃ ርቀት ያህል መራቅ፣
- አይንና አፍንጫን እጅን ሳይታጠብ አለመንካት፣
- በሚያነጥሱበት እና በሚያስሉበት ጊዜ አፍና አፍንጫን በሶፍት ወይም ክርንን አጥፈው በመጠቀም ወደ ሌሎች እንዳያስተላልፉ መጠንቀቅ፣
- የተጠቀሙበትን ሶፍትና ተመሳሳይ ነገሮች በቆሻሻ ክዳን ባላቸው ማጠራቀሚያ ማስወገድ፣
- በስራ ቦታ፣ በትራንስፖርት እና መኖሪያ ወይም የመኝታ ክፍል መስኮት በመክፈት በቂ አየር እንዲኖር ማድረግ፣
- በተለይ በባንካችን ቅርንጫፎች ውስጥ መጨናነቅን ለመቀነስ የሞባይል ባንኪንግ ኢንተርኔት ባንኪንግ የኤቲኤም እና የግብይት ማሽን አገልግሎት መጠቀም በዋነኝነት ይገኙበታል።

# Proverbs & Quotes

"Success usually comes to those who are too busy to be looking for it."
**- Henry David Thoreau**

"There's no shortage of remarkable ideas, what's missing is the will to execute them."
**- Seth Godin**

"Forget past mistakes. Forget failures. Forget everything except what you're going to do now and do it."
**- William Durant**

"There are no secrets to success. It is the result of preparation, hard work and learning from failure."
**- Colin Powell**

# Photo Reel








Pictorial Memories of the 25th General Shareholders' Assembly

# Photo Reel










ለማንኛውም ፍላጎትዎ
በ 8980
የደንበኞች አገልግሎት መስመር ይደውሉ
24
HOURS
አዋሽ ባንክ
AwashBank